
ከድኅነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ
3ኛ ዙር ተከታታይ ዕትም፣ ቁጥር 5

# ተፈራ ደግፌ

## የባንክ እድገት ለአገሪቱ ልማት ያደረገው አስተዋጽኦ



የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ)



**ከድህነት ወደ ልማት፦ ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ**
**3ኛ ዙር፡ ተከታታይ ዕትም፣ ቁጥር 5**

# *ተፈራ ደግፌ*

## የባንክ እድገት ለአገሪቱ ልማት ያደረገው አስተዋጽኦ

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ
አዲስ አበባ

**© ኅዳር 2000 የደራሲውና የማኅበራዊ ጥናት መድረክ**

**በአዲስ አበባ የታተመ**

**አድራሻ:**

**የማኅበራዊ ጥናት መድረክ**
**ፖ.ሣ.ቁ. 25864 ኮድ 1000**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

**ስልክ**፡ (251-11) 157-2990/91
**ፋክስ**፡ (251-11) 157-2979
**ኢ.ሜይል**: fss@ethionet.et
**ድረ-ገጽ**፡ www.fssethiopia.org.et

**© 2000 የማኅበራዊ ጥናት መድረክ**

**የሽፋንና የገጽ ዲዛይን፡- ቆንጅት በለጠ**

**ISBN 10: 99944-50-18-2**
**ISBN 13: 978-99944-50-18-3**

ይህ ጽሑፍ የታተመው ከኖርዌይ ቤተ ክርስቲያን እርዳታ ድርጅት ፣ ከዴንማርክ ኤምባሲ፣ ከአየርላንድ ኤምባሲና ከእንግሊዝ ዓለም-አቀፍ የተራድዖ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የማጥመን፣ የሥራ አመራር ቦርዱን ወይም የማጥመን አጋሮች አመለካከት ሳያንፀባርቁ ይችላሉ፡፡

# ማውጫ


**የመክፈቻ ንግግር......................................................................V**

1. የባንክ እድገት ለአገሪቱ ልማት ያደረገው አስተዋጽኦ ............................... 1

2. *የመጀመሪያ ትምህርት* .................................................................... 2

3. *የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ አመሰራረት* .............................................. 4

4. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መቋቋም ............................................................ 13

5. የንግድ ባንክ ጥገኛ ድርጅቶች....................................................... 21

6. የነበረው የኢኮኖሚና የንግድ ሁኔታ ................................................. 24

**መደምደሚያ** ................................................................................ 26

## የመክፈቻ ንግግር

### *ሺፈራው በቀለ*

**የተከበራችሁ እንግዶቻችን፣**

*አቶ ተፈራ ደግፌ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው የመጀመሪያ የባንክ ባለሙያዎች ውስጥ አንዱ ናቸው። በዚህ ሙያ እጅግ ከፍ ያለ ታዋቂነትና ተከባሪነትን አግኝተዋል። በ1966 ዓ.ም. በካናዳ /ቫንኩቨር/ የሚገኘው የብሪቲሽ ኮሎምብያ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በህግ ሰጥቷቸዋል። የደርግ መንግሥት በ1968 ዓ/ም ባሰራቸው ጊዜ* The New York Times *ጉዳዩን እ.ኤ.አ. በፌብሩዋሪ 26 ቀን 1976 በወጣው እትሙ ላይ ዘግቦት ነበር። ይኸው ታላቅ ጋዜጣ በጁን 10 ቀን 1976 ባወጣው እትሙ ሲጽፍ አቶ ተፈራን «ዝነኛው ሰው»* (Prestigious figure) *ካላቸው በኋላ መታሰራቸው አለአግባብ እንደነበር ጽፎ ነበር። ምንም ታዋቂ ሰው ቢሆኑ ደርግ ለአያሌ አመታት አሠራቸው- ያለምንም ጥፋት!*

*ያገር ተወላጅ የባንክ ባለሙያዎችን ለማፍራት ኢትዮጵያ ረጅም መንገድ ተጉዛለች። በ1897 ዓ.ም. የመጀመሪያው ባንክ (የግብጽ ባንክ አካል የነበረው የአበሻ ባንክ) ሲከፈት አገራችን የሂሳብ ትምህርት እንኳ የነበረው አንድም ሰው አልነበራትም። እስከ 1928 ዓ.ም. ድረስ የባንክ ሥራ በውጭ ሰዎች ነበር የሚካሄደው። ከጠላትም ነጻ ከወጣች በኋላ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ጊዜ ወስዶባታል። ይሁንና የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን የባንክ ባለሙያዎች በሙያቸው እጅግ የላቁ ነበሩ። በአለም አቀፍ ደረጃ ለረጅም ጊዜ ተከባነሪት ያገኙ ነበሩ።*

*በአቶ ተፈራ አመራር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሰፍቷል፤ ተመንድጓል። ለአገሪቷ ልማትም እጅግ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህ ጽሁፋቸው አቶ ተፈራ ከጅምሩ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ የባንክ ተቋም ያደረገውን እድገት ይተርካሉ። ችግሮቹንና ስኬቶቹን ያቀርባሉ። የራሳቸውን ልምድም ስላካተቱበት ትረካው ወጥነት አግኝቷል።*

# የባንክ እድገት ለአገሪቱ ልማት ያደረገው አስተዋጽኦ

*ተፈራ ደግፌ*

## *1. መግቢያ*

የማኀበራዊ ጥናት መድረክ ባዘጋጀው "ከድህነት ወደ ልማት እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ" በሚል ርዕስ የባንክ ዕድገት ለአገሪቱ ልማት ስለአደረገው አስተዋጽኦ ንግግር አድርጌ ድርሻዬን እንድወጣው ባዘጋጆቹ በመጋበዜ ደስታ ይሰማኛል።

በበኩሌ ከኢትዮጵያ ባንኮች አገልግሎት ከተለየሁ ከሰላሳ ዓመት በላይ ሆኗል። ስለዚህ በዚህ ዓመታት ርቀት በዚህ ዓቢይ ርዕስ ስለአገራችን ባንክ ልምድ በአነስተኛ እውቀቴና በደከመ ጉልበቴ ምን ላካፍል እችላለሁ በማለት ወደ ኋላ ብዬ ነበር። ነገር ግን የማከብራቸው የፕሮግራሙ አዘጋጆች በተለይ ፕሮፌሰር ሽፈራው በቀለ የቀድሞው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እድገት ልምድ ለመጪው ትውልድ በጣም ይጠቅማል በማለት አደፋፈሩኝ።

እንደሚታወቀው ለመጀመሪያ ጊዜ ባንክ ኢትዮጵያ የተቋቋመው በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት በ1898 ዓ.ም. ነው። ይህ "ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ" (የዛሬው ዘመናዊ ባንክ ሳይሆን) አጼ ምኒሊክ በእንግሊዞች ትብብር ተቋቋሞ በ1923 ዓመት ገደማ በኢትዮጵያ ባንክ የተተካው ነው። ከነፃነት ማግስት ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ተቋቋመ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተተኪ ወራሽ ድርጅት ሆኖ ቀጠለ።

እኛ ያለፍንበት ዘመን ከአሁኑ ጋር ሲተያይ ብዙ ልዩነት አለው። አያሌ ዓመታት ስለአለፉ ብዙ ለውጥም ስለተደረገ ውጤቱን ማወዳደር ያስቸግራል። በእኛ ጊዜ ባንኮች እየተወዳደሩ የሚሰሩት አብዛኛውን በርሳቸው ውሳኔ ነበር። የብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር ብዙውን ጊዜ የሚፈጸመው ከባንኮቹ ጋር በመመካከርና በመግባባት ነበር።

በዚህ ዓይነት ነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጽኑ መሰረት ሊዋቀር የበቃው።

ስለዚህ ዛሬ የማደርገው ንግግር የሚያተኩረው በ1934 ዓ.ም. ከተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ ጀምሮ ወራሹ ድርጅት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያደረገውን አስደናቂ እድገት የሚገልጽ ነው። በኢትዮጵያ ባንኮች ውስጥ የፈጸምኩት አገልግሎት ከ1934 እስከ 1968 ዓ.ም. ድረስ በመሆኑ ንግግሬ ከነዚህ ዓመታት አያልፍም።

## 2. የመጀመሪያ ትምህርት

የተወለድኩት ሰኔ 8 ቀን 1918 ዓ.ም. ሸዋ ጠቅላይ ግዛት አንኮበር አውራጃ አንበሴ በሚባል ቀበሌ ነው። አባቴ አቶ ደግፌ በላይነህ እናቴ ወይዘሮ እርገጫቸው (እማማ እታባ) ገብረ ማርያም ናቸው። የአደግሁት ገንዳውሃ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ ነው።

ሰባት ዓመት ገደማ ሲሆነኝ ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ታላቋ አክስቴ ወይዘሮ ጌጤ ገብረማርያም ዘንድ አረፍኩ። አንድ ቄስ ቤት ፊደል ከቆጠርኩ በኋላ አሊያንስ ፍራንሴዝ በሚባል የፈረንሳይኛ ትምህርት ቤት ገብቼ ዘመናዊ ትምህርት ጀመርኩ።

ሁለት ዓመት ያህል እንደተማርኩ በ1928 ዓ.ም. ፋሺስት ኢጣሊያ አገራችንን ከወረረ በኋላ የአሊያንስ ፍራንሴዝ ትምህርት ቤት ስለተዘጋ ትምህርቴ ተቋርጦ ቀረ።

በአምስቱ የፋሺስት ኢጣሊያ ወራራ ዘመን ጥገኛ ሆኜ የኖርኩት ሌቭድሮዝደቭስኪ የሚባሉ የመስኮብ ስደተኛ ጄኔራል ቤት ነው። ልጃቸው ማዳም አሌክሳንድራ ዳቤራት የታወቁ የጥርስ ሐኪም ነበሩ። በተላላኪነት ጥቃቅን ሥራ በመሥራትና ልጃቸውንም በማጫወት ነው ያደግሁት። ከልጃቸው ጋር በመማር መስኮብኛና ኢጣሊያንኛ ቋንቋ ለመማር በቃሁ። በነዚህም ቋንቋዎች ብዙ መጽሐፍት ለማንበብ ቻልኩ።

በ1933 ዓ.ም. በታላቋ ብሪታኒያ ጦር ዕርዳታ ነጻነታችን ከተመለሰ በኋላ የሚረዱኝ የፈረንጅ ቤተሰብ በሙሉ በጠላትነት ከአገር ስለተጋዙ መጠጊያ አጣሁ። የትምህርትም ዕድል ስላልገጠመኝ ሥራ ፈልጌ ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ በአስተርጓሚነት ተቀጠርኩ። በዚያን ጊዜ የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ሚሽል ባንኩል የሚባሉ የመስኮብ ስደተኛ ነበሩ። አንድ ዓመት ያህል ሲንጀር ኩባንያ እንደሰራሁ የመማር ጉጉት ስለነበረኝ ሥራውን ለመተው ወሰንኩ።

አጋጣሚ ሆኖ አዲስ የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ (State Bank of Ethiopia) ቋንቋ የሚያውቁ ሠራተኞች እየፈለገ ይቀጥራል ሲባል ሰምቼ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ማመልከቻ አቀረብኩ። በቀጠሮው ዕለት ሚስተር ሐይሊግ የሚባሉ ተባባሪ ሥራ አስኪያጅ አነጋገሩኝ። ሚስተር ሐይሊግ የሃንጋሪ ተወላጅ መስኮብ ቤተሰብ ዘንድ ስሠራ ያውቁኝ ስለነበረ ያለአንዳች ውዝግብ ባንክ እንድቀጠር ፈቀዱ። በ1936 ዓ.ም. በ18 ዓመቴ በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ በጸሐፊነት (Filing Clerk) ተቀጠርኩ። ሥራ ስጀምር ነው የማላውቀው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቅ ያለው። ወዲያውኑ ከጓደኞቼ ጋር ተሰብስበን በብሪቲሽ ካውንስል በተከፈተው ብሪቲሽ ኢንስቲቱት በተባለው የማታ ትምህርት ቤት እንግሊዘኛ ለመማር ተመዘገብን። ባንክ አንድ ዓመት ተኩል ከሠራሁ በኋላ ከሌሎች ወጣት ሠራተኞች ጋር ተመርጬ ትምህርቴን ለማሻሻል ኮተቤ ወደሚገኘው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተላክሁ። በየጊዜው ልዩ ፈተና እየተሰጠን የለብ ለብ ትምህርትን ለአንድ አመት ወስጄ በመንግስት ባንክ ስኮላርሺፕ ለከፍተኛ ትምህርት ካናዳ እንድላክ ተወሰነ።

ስለዚህ በ1938 ዓ.ም. ለከፍተኛ ትምህርት ካናዳ ከተላኩት የመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች አንዱ ነበርኩ። መጀመሪያ ያመራሁት ካልጋሪ አልበርታ ወደሚገኘው የንግድ ኮሌጅ (GARBUTT BUSINESS COLLEGE) ነበር። ባንድ ዓመት ውስጥ ትምህርቱን ጨርሼ ዲፕሎማ ለመቀዳጀት በቃሁ። ወዲያውኑ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን ለመቀጠል ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ (UBC) በ1939 ዓ.ም. ተመዘገብኩ። ኮመርስ ፋኩልቱ በየአመቱ የበጋ

ትምህርት ጭምር እየወሰድኩ በ1942 ዓ.ም. ቢ.ኮም ዲግሪ ተቀበልኩ። አንድ ሁለት ዓመት የሕግ ትምርህት ተከታትዬ በ1945 ዓ.ም. አገሬ ተመልሼ የባንክ አገልግሎቴን ቀጠልኩ። በ1945 ዓ.ም. አገሬ ተመልሼ የረዥም ጊዜ የባንክ አገልግሎቴን የጀመርኩበት ዘመን መሆኑን በትዝታ አስታውሳለሁ። አገር ውስጥና ጎረቤት አገርም በሚገኙ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ መሥሪያ ቤት በጸሐፊነት ደረጃ ጀምሬ የባንኩ ነገረ ፈጅ በመሆን፤ በ1953 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራ አስኪያጅ ለመሆን በቃሁ። ከ1956 እስከ 1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ ከ1966 እስከ 1968 ዓ.ም. ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዋና አዛዥ በመሆን አገልግያለሁ።

## 3. የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ አመሰራረት

እኔ ተቀጥሬ የባንክ ሥራ የጀመርሁበትን ሁኔታ ከገለጽኩ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እንዴት እንደተቋቋመ መግለጽ አስፈላጊ ይመስለኛል። የኢጣሊያን ወረራ ተወግዶ ነጻነት ከተመለሰ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደገና በመቋቋም ላይ ሳለ የባንክና የገንዘብ ስርጭት ከእንግሊዝ የምሥራቅ አፍሪቃው የቅኝ አገዛዝ ጋር አቀላቅሎ ለማስተዳደር የእንግሊዝ ግፊት ነበር። ኢትዮጵያ ተነጥላ የራሷን ባንክ ለማቋቋም ስትነሳ ብዙ ችግር ገጥሟት ነበር።

ይህንን ችግር በውስጥ ምክርና ድፍረት ተወጥቶ ነው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ አጭር አዋጅ ተረቅቆ በ1934 ዓ.ም. ታውጆ ባንኩ የተቋቋመው። በዓመቱ ሠራተኛው ተሰባስቦ ሥራውን ለመጀመር በቃ። በጦርነቱ ጊዜ የታላቋ ብሪታኒያን የጦር ሠራዊት ተከትሎ መጥቶ የኢጣሊያን ባንኮችን አስወግዶ የባንኩን ሥራ ተረክቦ የሚያስተዳድረው ባርክሌይስ ባንክ (BARCLAYS BANK D.C.&O) ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ይህንን የእንግሊዝ ባንክ ተክቶ ነው ሥራውን የጀመረው። ባንኩ የተዋቀረው የጠቅላይ (ማዕከላዊ) ባንክንና የንግድ ባንክን ሥራ አጣምሮ እንዲሠራ ነው። ሥራውን ሲጀምር አብዛኞቹ የባንኩ ሠራተኞች የውጪ አገር ዜጎች ነበሩ። ብዙዎቹ ከኢጣሊያን ወረራ በፊት የቀድሞው የኢትዮጵያ ባንክ

ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩ ናቸው። በእኛ ጊዜ ሠራተኛው ሲቀጠር ስልጠናና ማለማመጃ ሥርዓት አልነበረም። ሠራተኛ እየሠራ ሌላውን እያየ ነበር የሚለማመደው። ሁሉም ስለሚተዋወቅ መረዳዳት፣ በሥራው ውጤት መተባበር ፣ የማወቅ ፍላጎት ጎልቶ ይታይ ነበር። ሁላችንም የመማር ጉጉት ስለነበረን በራሳችን ወጪ ከካይሮ ድረስ በፖስታ የመላላክ ትምህርት ሂሳብ እንማር ነበር። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እውቀታችን ደካማ ስለነበር የሚያውቀው የማያውቀውን ይረዳ ነበር። በዚህ ዓይነት የባንኩ ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድ የገጠር ቅርንጫፎች መከፈት ጀመሩ። የእነዚህ ቅርንጫፎች ኃላፊዎችም የውጭ ዜጎች ነበሩ። ተራ ሠራተኞቹ ግን ሥራውን የሚለማመዱ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በ1937 ዓ.ም. አሜሪካን አገር በሚስጥር ተዘጋጅቶ አዲስ የኢትዮጵያ ብር ገንዘብ ታውጆ ወጣ። በዚህ ዓይነት ነው የኢጣሊያ ሊሬ፣ የምስራቅ አፍሪካ ሺሊንግ በአዲሱ የኢትዮጵያ ብር የተለወጠው። የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የባንክ ሥራው ቀስ በቀስ ነው እየሰመረ የሄደው። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ከባንክ ውጭ ለገንዘብ ሚኒስቴር ብዙ ልዩ ልዩ አገልግሎት አበርክቷል። አዲስ አበባ፣ ጂቡቲ፣ አሰብ የባሕር ትራንዚት አገልግሎት ይሠራ ነበር። የሊጋሃር ጉምሩክ መጋዘን ያስተዳድር ነበር። አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ከፍቶ ለትምባሆ ሞኖፖል ሲጃራ በካርቶን ያከፋፍል ነበር። በአስረኛ ዓመቱ ነው የባንክ ስልጣኑ በአዋጅ እየተጠናከረ ሲሄድ ወደ ዋናው የባንክ ተግባሩ የዞረው። ቅርንጫፎች በጠቅላይ ግዛት ዋና ዋና ከተሞች ተከፈቱ፤ በዚህ ዓይነት የባንክ አገልግሎት በመጠኑ መሰራጨት ጀመረ። በዚያን ጊዜ አብዛኞቹ የባንኩ ደንበኞች የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። በብድርም በኩል አብዛኛው መንግሥት ነክና በውጭ አገር ሀብት የተቋቋሙ ድርጅቶች ነበሩ።

## 3.1 የባንኩ ስልጠና መስፋፋት

በ1937 ዓ.ም. የሕጋዊ ገንዘብ አዋጅ እንዳወጣ ባንኩ ባለሙሉ ሥልጣን ብቸኛ የኢትዮጵያ ብር አሳታሚና አከፋፋይ ሲሆን የብሔራዊ ባንክ ሥልጣንን ተጎናጸፈ። ከዚህ ቀጥሎ ነው በኅዳር 21

ቀን 1939 ዓ.ም. በወጣ አዋጅ መሰረት የማሪያ ቴሬዛ ብር ያለው ሁሉ ባንክ እያቀረበ እንዲመነዝር የታዘዘው።



ምንዛሪው አንድ ማሪያ ቴሬዛ ብር በአንድ ተኩል የኢትዮጵያ ብር ነበር። እንዲሁም ከነሐሴ ወር ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ የውጪ ምንዛሪ (foreign exchange) ብቸኛ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሆነ። ቀጥሎም የአገር ውስጥና የውጭ አገር ንግድ መስፋፋት ጀመረ። ዋናው የውጭ ንግድ የሚካሄደው በጅቡቲና በኤደን ባንኮች ያለው ሁሉ በባንክ በኩል ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እንደ ንግድ ባንክ ሆኖ ሲሠራ መጀመሪያ የሚሰጠው አገልግሎት የተንቀሳቃሽ ሂሳብና የገንዘብ ማዛወር/ማስተላለፍ ሥራ ነበር። ሥራው እየደረጀ ሲሄድ ነው ተደራቢ ሥልጣን የተሰጠው። በ1938 ዓመተ ምህረት ነው የቁጠባ ሂሳብ (Saving Account) አገልግሎት የጀመረው:: የባንኩን ሥራ ለህዝቡ ለማለማመድ በባንኩ እምነትን ለመፍጠር ብዙ ዓመት ፈጅቷል። ገንዘቡን በጉድጓድ እየቀበረ ማስቀመጥ የለመደን ኅብረተሰብ ቀሰ በቀስ እየመከሩ ባንክ ላስቀምጥልህ ብሎ ማግባባት ቀላል አልነበረም። ብድርን በሚመለከት ደግሞ ንብረቱን አስይዞ

መበደር የሚፈራውን ጀማሪ ነጋዴ ማሳመን፣ ገንዘብን በባንክ በኩል ማስተላለፍ ማስለመድ ከፍተኛ ትግል ነበር። ዘመናዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲጀምር ትምህርትም እየተስፋፋ ሲሄድ ኢትዮጵያውያን ሥራውን እየተላመዱ የባንኩን አመራር ሥራ እስከመያዝ በቁ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሁለገብ ድርጅት ሆኖ ጠቅላላ የባንክ አገልግሎትን ማስፋፋት ጀመረ። የማዕከላዊ ባንክ ሥራው የተወሰነ ነበር። ምክንያቱም አገር ውስጥ ይሠሩ የነበሩት የውጭ አገር ባንኮች አነስተኛ ነበሩ። አንዱ አዲስ አበባ ተቋቁሞ የነበረው የፈረንሳይ ባንክ ደ ሊንዶሽን (BANKQUE DE L'INDOCHINE) የወኪል ጽሕፈት ቤት ነው። ሁለት ሌሎች ባንኮች አስመራ የነበሩት ባንኮ ዲ ሮማ (BANCO DI ROMA) እና ባንኮ ዲ ናፖሊ (BANCO DI NAPOLI) የውጭ አገር የባንክ ቅርንጫፎች ነበሩ። የእነዚህ አነስተኛ ድርጅቶች የባንክ ሥራ በጣም የተወሰነ በመሆኑ የመንግሥቱ ባንክ የቁጥጥር ሥራ ቀላል ነበር።

ሌላው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ተግባር የመንግሥቱ ተጠሪ ወኪል ሆኖ የመሥራት ሥልጣን ነበረው፤ ይኸውም በመንግሥት ስም ተቀማጭ ገንዘብ መቀበልና መክፈል ነበር። ሲያስፈልግ ደግሞ ብድር የመስጠት ስልጣን ነበር። ባንኩ ገንዘብ የማሳተምና የማሰራጨት፤ የሀገሪቱን የውጪ ምንዛሪ የመቆጣጠርና የማስተዳደር ተግባር ነበረው። በዚህ አይነት ነው የንግድ ባንክና የማዕከላዊ ባንክ ሥራውን አጣምሮ ለሀያ አመታት ሲሠራ የቆየው።

## 3.2 የካርቱም ቅርንጫፍ መከፈት

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ውጭ አገር የሚሠሩ ሁለት ቅርንጫፎች ነበሩት። የመጀመሪያው የትራንዚት ሥራ የሚሠራ የጂቡቲ ቅርንጫፍ ነበር። ሁለተኛው ለባንክ አገልግሎት ሱዳን አገር የተቋቋመው የካርቱም ቅርንጫፍ ነበር።

የባንኩ ቅርንጫፍ አመሰራረትና ይሰጠው የነበረ የባንክ አገልግሎት እንዴት እንደተቋቋመ ባጭሩ ለመግለጽ ያስቸግራል። መነሻው በክቡር አቶ ጌታሁን ተሰማ (በዚያን ጊዜ የንግድና የኢንዱስትሪ

ምክትል ሚኒስትር የነበሩ) የሚመራ የንግድ ልዑካን እኤአ በ1957 ወደ ሱዳን መላክ ነው። እኔም የልዑካኑ አባል ሆኜ ሄድኩ። የልዑካኑ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የነበረው ንግድ የሚዳብርበትን ዕቅድ ለማጥናትና የንግድ ውል ለመደራደር ስለነበረ ለዚህ ዓላማ ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ቅርንጫፍ ካርቱም ቢከፈት የሁለቱ አገሮች የጋራ ንግድ እንደሚረዳ ታምኖበት ጥያቄው ቀረበ። የሱዳን መንግሥትም የኢትዮጵያ ባንክ ቅርንጫፍ ካርቱም እንዲቋቋም ፈቀደ።

የንግድ ልዑካኑ ሪፖርት ቀርቦ ከተፈቀደ በኋላ ለታቀደው የባንክ ቅርንጫፍ ብቁ የሆነ የሥራ አስኪያጅ በአስቸኳይ ተመርጦ እንዲቀጠር ባንኩ ታዘዘ። በጊዜው የነበሩት አሜሪካዊ የባንኩ ገዥ ሚስተር ጆርጅ ሬይ (GEORGE REA) በሥራው የሰለጠነ ኢትዮጵያዊ የለም በማለት የአንድ እንግሊዝ ዜጋ ስም አቀረቡ። ለታቀደው ዓላማ የውጭ ዜጋ አይበጅም ተብሎ የባንኩ ምርጫ ውድቅ ሆነ።

በዚያን ጊዜ እኔ የሲቪል አቪዬሽን ዋና ዲሬክተር ሆኜ ስሥራ ነበር። ከዚያ ተፈልጌ ነው የካርቱም ቅርንጫፍ የባንኩ ሥራ አስኪያጅ ተብዬ በጽሕፈት ሚኒስቴር ማዘዣ የተሾምሁት። ከዚያም በኋላ ከምክትል ሥራ አስኪያጁ ከአቶ ከበደ ሠረቀ ብርሃን ጋር ሆነን ቅርንጫፉን ለማቋቋም ሱዳን ተላክን። ካርቱም እንደደርስን በከተማው መሐል አዲስ የሚሠራ ሕንፃ ውስጥ ቅርንጫፉን ለማቋቋም የውል ድርድር ጀመርን።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የንግዱ ክፍል ቅርንጫፍ ካርቱም የተከፈተው በ1950 ዓ.ም. ከዋናው መሥሪያ ቤት አራት ኢትዮጵያውያን ኃላፊዎች ተመርጠው ተልከው ነው። ለቅርንጫፉ የሚስማሙ ሱዳናውያን እየመለመልን ቀጥረን ማሰልጠን ጀመርን፤ በተቻለ መጠን የባንኩ ገጽታ አፍሪቃዊ እንዲሆን ጥረት አደረግን። ባጭር ጊዜ ብዙ ደንበኞች አፍርተን ባንኩ ተወዳጅ ሆነ። ካርቱም የሚኖሩ ብዙ ኤርትራዊ ወይዛዝርት ስለነበሩ የቅርንጫፉ ደንበኞች ሆኑ። የባንኩ ሙሉ ስም ለአረብኛ ተናጋሪዎች ስለሚያስቸግር

ደንበኞቻችን ቅርንጫፉን በወዳጃዊ አጠራር "ባንክ ኤል ሐበሺ" ብለው ሰየሙት።

በዚያን ጊዜ ሱዳን ውስጥ ስድስት የውጭ አገር ባንኮች ነበሩ። ሦስቱ የምዕራባውያን ባንኮች-ማለት ባርክሌይስ ባንክ፣ ኦቶማን ባንክና ክሬዲሊዮኔ ነበሩ። የመካከለኛው ምሥራቅ ባንኮች ደግሞ የአረብ ባንክ፣ ባንክ ምስርና የሱዳን ንግድ ባንክ ነበሩ። የግብፅ ብሔራዊ ባንክ (The National Bank of Egypt) ሱዳን የማዕከላዊ ባንክ ተግባርን ሲሠራ ቆይቶ በሱዳን ባንክ ተተካ። ብቸኛው አፍሪካዊ የእኛ ቅርንጫፍ ነበር። እነዚህን የደረጁ ባንኮች እየተወዳደረ ነው የእኛ ባንክ በሦስት ዓመታት ውስጥ ብዙ ደምበኞች ለማፍራትና አትራፊ ለመሆን የበቃው።

የባንካችን የካርቱም ቅርንጫፍ ለኢትዮጵያ የባንክ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የባንክ ውድድር ሥራ ለአገር ልማትና ለኢኮኖሚ እድገት ምን ያህል እንደሚጠቅም ራሳችን እየሠራን ነው የተማርነው። ስለዚህ በ1960ና በ1970ዎቹ አስርት ዓመታት በአገር ውስጥ ለባንክ አመራር ብቁ ሆነው ያገለገሉ አብዛኞቹ ኢትዮጵያዊ የባንክ ባለሞያዎችና ኃላፊዎች ካርቱም ቅርንጫፍ እየሠሩ በቂ ልምምድ ያገኙ ናቸው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ማንሳት ይበቃል። ከበደ ሠረቀብርሃን፣ መስፍን በለጠ፣ ታደሰ አበበ፣ ስሜ ታከለ፣ ቸርነት በየነ፣ ተሳለ ወርቁ፣ ኢማም ቢ. ፊሎውስ፣ ጌታቸው ደስታ፣ ወይዘሮ በላይነሽ ማንደፍሮ ነበሩ። ሁሉም ታዋቂ የባንክ ባለሙያዎች ሆነው እያንዳንዳቸው በብሔራዊ ባንክና በንግድ ባንክ ውስጥ ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ የደረሱ ናቸው።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የካርቱም ቅርንጫፍ አስር ዓመት ያህል ካገለገለ በኋላ በጄኔራል ኒሜሪ ዘመነ መንግሥት እኤአ በ1969 የግል ባንኮች ሁሉ በሱዳን መንግሥት ሲወረሱ የእኛም ቅርንጫፍ አብሮ ተወረሰ።

## 3.3 ባንኩን የውጭ አገር ዜጎች ሲያስተዳድሩት

አሁን ስልሳ አራት ዓመታት ካለፉ በኋላ ወደ ኋላ እየተመለከቱ ሁኔታዎችን በትክክል እያነጻጸሩ ማስረዳቱ ያስቸግራል። በጠቅላላው እኤአ ከ1942 አንስቶ እስከ 1959 ዓመተ ምህረት ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ገዢዎች የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። የሚመጡት በልዩ የሥራ ኮንትራት እየተቀጠሩ ነበር። የባንኩ የሥራ አስፈጻሚና የውስጥ አስተዳዳሪዎችም የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። ኢትዮጵያውያን በከፊል ስልጣን መጋራት የተጀመረው አቶ የወንድ ወሰን መንገሻ ምክትል ገዥ ሆነው በ1959 ዓመተ ምህረት ሲሾሙ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክን ያገለገሉት የውጭ አገር ዜጎች የሚከተሉት ናቸው፡-

| | |
|---|---|
| ሚስተር ሲ. ኤስ. ኮሊየር | 1942-1943 |
| ሚስተር ጆርጅ ኤ. ብርላወርስ | 1949-1952 |
| ሚስተር ጃክ ቤኔት | 1944-1948 |
| ሚስተር ደብልዩ ኤች ሮዜል | 1953-1955 |
| ሚስተር ኒል ፔሪ | 1955 |
| ሚስተር ጆርጅ ሬይ | 1956-1959 |

በ1960 ዓመት ክቡር አቶ ምናሴ ለማ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ተጠባባቂ ገዥ ሆነው ተሾሙ (በወቅቱ የመንግሥት ኦዲተር ነበሩ)። የባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ኢግናሲዩስ ሜንዚስ የሚባሉ የሕንድ ተወላጅ ነበሩ። የባንኩን የውስጥ አስተዳደርም በኢትዮጵያውያን ለማስጨበጥ ታስቦ በ1953 ዓመተ ምህረት አጋማሽ ላይ እኔ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኜ በመሾም የተካሁት እኚሁኑ ሕንዳዊ ሥራ አስኪያጅ ነው። ከዚህ ጊዜ አንስቶ ነው የባንኩ ሥራ አስኪያጆች ሁሉ በኢትዮጵያውያን መተካት የጀመሩት።

በየድርጅቱ ብዙ የውጭ አገር ዜጎች ስለነበሩ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክን ለመምራት ብቁ አይደሉም የሚሉ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን ከተረከብን በኋላ ሥራው ሳይዛነፍ

በደንብ መቀጠሉ ብዙዎችን ሳያስደንቅ አልቀረም። እርግጥ ነው የውጭ ዜጎች የሆኑ አማካሪዎችና አንዳንድ ረዳቶች ነበሩ። በባንኩ ድጋፍ አዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያው የአክሲዮኖችና የገንዘብ ሰነዶች መሻሻጫ ገበያ ተቋቋመ። የባንኩ ዓመታዊ ሪፖርት መግለጫ ተሻሽሎ መታተም ጀመረ። ስለዚህ የብድር እድገት፣ የቅርንጫፎች መስፋፋት፣ የዓመት ገቢው ከፍተኛ እድገት በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የታየው በመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት ማለት በ1953፣ በ1954 እና በ1955 ባንኩ በኢትዮጵያዊያን የበላይ መሪነት በሚካሄድበት ዘመን ነበር።

የአገር ውስጥ ንግድ መንቀሳቀስ ሲጀምር ልማቱን ለማበረታታት ቀስ በቀስ የባንክ አገልግሎትም በየከተማው በመጠኑ መሰራጨት ጀመረ። የተሟላ የባንክ አገልግሎት በአዲስ መልክ ለመቋቋም እቅድ ወጣ። ይህ የባንክን አቋም የማሻሻል እቅድ ሰፊ ጥናት እንደሚያስፈልገው ታውቆ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (International Monetary Fund) አንድ አዋቂ ተቀጥሮ በገለልተኝነት የአገሪቱን ሁኔታ ካጠና በኋላ በዓመቱ ጥናቱ ተጠናቆ ቀረበ። የቀረበው ጥናት ያሳሰበው አገሪቱ ውስጥ የባንክ አገልግሎት እንዲስፋፋ ከተፈለገ የግል ባንኮች መቋቋም አስፈላጊ ስለሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የባንክ ሞኖፖል መለወጥ አለበት ተባለ። በዚህ አሳብ መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሁለት ተከፍሎ አንዱ ማዕከላዊ ባንክ ሌላው ደግሞ የንግድ ባንክ እንዲቋቋሙ ተወሰነ። ቀጥሎም አዲስ የባንክ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለፓርላማ ቀረበና "ስለገንዘብና የባንክ ሥራ አዋጅ" በሐምሌ ወር በ1955 ዓ.ም. ታውጆ ወጣ።

## 3.4 የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ ስሁስት መከፈል

አዲሱ የባንክ አዋጅ የወጣው በሐምሌ ወር 1955 ዓ.ም. ስለሆነ የመንግስት ባንክ ሀብትና ሠራተኛ በሁለቱ ድርጅቶች መሐከል ተደላድሎ በስድስቱ ወር ውስጥ ተጠናቀቀ።

ሀ/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የጠቅላይ (ማዕከላዊ) ባንክ ሥራን ሁሉ አጠቃልሎ እንዲሠራ በልዩ አዋጅ ተቋቋመ።

ከኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ንብረት ውስጥ በአዋጅ ተከፍሎ ለብሔራዊ ባንክ ከተላለፈው ንብረት ሌላ የንግድ ባንክ ድርሻ ሆነ።

ለ/ ከ1943 እስከ 1963 (ከ1936 እስከ 1955 ዓ.ም) የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሲሠራቸው የቆየውን የንግድ ባንክ ተግባሮች በንግድ ሕግ መሠረት ግላዊ ማኅበር ሆኖ በተቋቋመ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ (አክሲዮን ማኅበር) እንዲሠራው ተደረገ። በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ባንክ ባለአክሲዮኖች አምስት ነበሩ። ዋናው የገንዘብ ሚኒስቴር ሆኖ አራቱ ደግሞ መንግሥታዊ ድርጅቶች ነበሩ። በአዋጅ ለብሔራዊ ባንክ ከተላለፈው ውጪ የቀረው የባንኩ ንብረት ስልጣን ጥቅምና ልዩ መብት ሁሉ በወራሽነት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተላልፏል። በዚህ መሠረት አዲስ አበባ የሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤትና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በሙሉ ከነሂሳባቸው ወደ ንግድ ባንክ ተዛውረዋል።

የመንግሥት ባንክ ንብረትና ሠራተኛ በሁለቱ አዲስ ድርጅቶች መሐከል ተደላድሎ ሲያልቅ፣ በታህሣሥ ወር በ1956 ዓ.ም. ክቡር አቶ ምናሴ ለማ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ ሆነው ተሾሙ። እኔ ደግሞ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅና የቦርድ አባል ሆኜ ተመረጥኩ። በተጨማሪ ለመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሁለቱ የመንግሥት ባንኮች ተባብረው እንዲሠሩ ታስቦ አቶ ምናሴና አቶ የወንድ ወሰን (የባንኩ ገዥና ምክትል ገዥ) የንግድ ባንክ የዲሬክተሮች የቦርድ፤ እኔ ደግሞ የብሔራዊ ባንክ የቦርድ አባልነቴን ለቅቄ ሌላ ሰው ተተካ። ክቡር አቶ ምናሴም የንግድ ባንክ ቦርድ አባልነትን በ1969 ዓመት ለቀቁ።

ብሔራዊ ባንክና የንግድ ባንክ በአዲስ መልክ ተለይተው ሥራቸውን የጀመሩት እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 1 ቀን 1964 ነው። በዚህ አይነት ነው የባንክ ሥራ በአገራችን ተደላድሎ ለመስፋፋት የበቃው። አዲሱ የባንክ አዋጅ በ1955 ዓመተ ምህረት እንደወጣ ወዲያውኑ የግል ባንኮች ማለት የአዲስ አበባ ባንክ፣ ባንኮ ዲ ሮማ (ኢትዮጵያ) እና ባንኮ ዲ ናፖሊ (ኢትዮጵያ) ለግል ባለአክሲዮኖች የግል አክሲዮን እንዲሸጡ ተፈቅዶላቸው እንዲቋቋሙ የተደረገው። የማንኛውም

የግል ባንክ ባለቤትነቱ ቢያንስ ቢያንስ አምሳ አንድ በመቶ (51%) ኢትዮጵያዊ እንዲሆን የባንኩ አዋጅ ያስገድደናል።

## *4. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መቋቋም*

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ1956 ዓ.ም. እንደ ግል ኩባንያ ሆኖ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ መሰረት ሲቋቋም የመሰረቱት አምስት ባለአክሲዮኖች ነበሩ። መስራቾቹም አምስት መንግሥታዊ ድርጅቶች ነበሩ። ዋናውን ድርሻ መንግሥትን ወክሎ የገንዘብ ሚኒስቴር ነው የያዘው። አራቱ ደግሞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራት ኃይል ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና የኢትዮጵያ ሲሚንቶ ኮርፖሬሽን እያንዳንዱ አንድ አክሲዮን ይዞ ባለቤት በመሆን ነበር። የባንኩ መነሻ ካፒታል 20,000,000 ብር ነበረ።

በግል መልክ የተቋቋመው መንግሥታዊው የንግድ ባንክ ከእነዚህ የግል ባንኮች ጎን ለጎን ነፃ በሆነው ውድድር መንፈስ ሥራውን እየተሻሙ የቀለጠፈ የባንክ አገልግሎት በማበርከት የአገሪቱ ኤኮኖሚ እንዲዳብር አስተዋጽኦ አድርጓል። በ1960ዎቹ አስርተ ዓመታት የአገሪቱ ኤኮኖሚ ሰፊ እድገት ያሳየበት ዘመን ነበር። ዘመናዊ የግል እርሻዎች የተስፋፉበት፣ ሰፋፊ የቡና ተክል የለማበት፣ እንዲሁም የቅባት እህል፣ ጥራጥሬ፣ ቡና በብዛት ወደ ውጭ አገር መላክ የጀመረበት ዘመን ነበር። በዚህ የአገሪቱ እድገት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።

ባንኩ በአዲስ መልክ ሥራውን እንደጀመረ ዋና እቅዱ ሠራተኞቹን ማሰልጠንና የባንክ ቅርንጫፎቹን ማስፋፋት ነበር። የቅርንጫፉ ማስፋፋት እቅድ ብዙ ድካምና ውጣ ውረድ ቢያስከትልም ከፍተኛ የግል ቁጠባ ሂሳብና ተቀማጭ ገንዘብ ለማሰባሰብ ረድቷል። እንደሚታወቀው የአገር ልማት እቅዶች ግባቸውን እንዲመቱ ከተፈለገ ሕዝባዊ ተሳትፎ ኅብረተሰባዊ ድጋፍና በቂ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ ነው። በ1960ዎቹ ዓመታት ከመንግሥታዊ ድጋፍ ጋር

የግል ዘርፍ እየተስፋፋ በመምጣቱ የአገር ውስጥና የውጭ ንግድ እንዲዳብር ባንኩ ረድቷል።

አርባ ዓመት ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስታውሰው በእኛ ዘመን ባንኩ በማደግ ላይ ስለነበረ ሠራተኛው በባንኩ የነበረውን እምነት ለማጠናከር በተቻለ መጠን ሠራተኛውን እያሰለጠነ የሚሾመው ከነባር ሠራተኛው እየተመረጠ ነበር። በዚያን ጊዜ በባንኩና በሠራተኛው መሐከል የነበረው ግንኙነት ጤናማ የአባትና የልጅ ግንኙነት መሰል ስለነበረ ባንኩ የሠራተኛውን የሥራ ብቃት ለማሳደግና የሙያ እድገት እንዲያገኝ ያስተምር፣ ያሰለጥንና ያበረታታ ነበር። በአጠቃላይ ሲታይ "እኔ ለድርጅቱ፤ ድርጅቱ ደግሞ ለእኔ" የሚል የመተሳሰብ ስሜት እንደነበረ በጊዜው የነበሩ ሠራተኞችና የባንኩ ደንበኞች ይመሰክራሉ፤ ያወሳሉ።

የባንኩ አስተዳደር በኢትዮጵያዊነቱ እየተመካ የሥራ ጥራቱን በማሻሻል ትጋትን፣ ትዕግስትን፣ ብቃትና ቆራጥነትን ለማንፀባረቅ ይጥር ነበር። በተቻለ መጠን እውነት፣ ጨዋነት፣ ታማኝነት እንዲሰፍን ጥረት ያደርግ ነበር። የዘወትር የሥራ አክብሮትና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት መከበር ዋና ዓላማው ነበር። ይህ ነው ባንኩ በጽኑ መሰረት እንዲገነባ የረዳው። ምርታማነቱን ከፍ ለማድረግ እንዲያስችለው ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን ማካሄድ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነበር። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንደተቋቋመ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረታችንን ለሟሟላት ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት የምንቀበላቸውን አዳዲስ ቅጥረኞችና ቀደም ሲል የነበሩትንም ሰራተኞች ከባንኩ አሰራር ጋር ለማስተዋወቅና አዳዲስ እውቀቶችና ብልሃቶች ለማስጨበጥ የሚረዳ የባንክ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል ከፍተን ነበር። ይህም የሰራተኞቻችንን የሙያ ብቃት በማሳደጉ ባንኩ በየጊዜው ላስመዘገባቸው ከፍተኛ የሥራ ውጤቶችና ዋናው ምክንያት ከመሆኑ ሌላ በሃገሪቱ ያሉትን የገንዘብና የመድን ተቋማት የሰው ኃይል እጥረት ለመሸፈን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉና በማድረግ ላይ መሆኑ የታወቀ ነው። ይህን መሰል ተቋም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ ሳይወሰን በኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በአውራ ጎዳና፣ በኢትዮጵያ መብራት ኃይል

ባለስልጣን፣ በቴሌኮሚዩኒኬሽንና በሌሎችም ድርጅቶች በመቋቋማቸው ፅኑና የማይናወጥ መሰረት ፈጥረውላቸዋል።

## 4.1 የሠራተኛው ስልጠና

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ከነጻነት ማግስት ሲመሰረት የተማረ ኢትዮጵያዊ አልነበረም። ለሥራው ተፈላጊ የነበረው የሰው ኃይል ከውጭ የተገኙ ሠራተኞች ስልጠና መሰረት የሆነው በ1938 ዓመተ ምህረት የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ወጣት ሠራተኞቹን መርጦ ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ሲልክ ነው። በዚያን ጊዜ ለትምህርት የተላኩት አስራ አንድ ሠራተኞች ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው። ወደ ካናዳ የተላክነው መጀመሪያ እኔ ከዚያም ቀጥሎ ተስፋዮሐንስ ሐጎስና ይላላ ይብሳ ነበሩ። ወደ ሲዊስ አገር በኋላ ወደ እንግሊዝ አገር የተዛወሩት አጥናፉ መንግሥቱ፣ ደበበ ሀብተዮሐንስ፣ መስፍን በለጠ፣ ታደሰ አበበ፣ ሥዩም አረሩ፣ ሥዩም ስብሐት፣ ነጋሳ ቶሌራና የሺጥላ አምበሉ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ተምረው ሲመለሱ ሦስቱ ወደ መንግሥት ሥራ ተደለደሉ። አምስቱ ደግሞ ማለት አጥናፉ፣ ደበበ፣መስፍን፣ታደሰና የሺጥላ በባንክ ሥራቸው ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ የባንክ ባለሙያ ናቸው። ካናዳም የተላክነው እንዲሁ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ የተላክንበትን ትምህርት አጠናቀን ስንመለስ ባንኩ አድጎ ሠራተኛው በርክቶ ቆየን። ስለዚህ ለቀረው ሠራተኛ ሁሉ ትምህርትና የባንክ ስልጠና እንዲያገኝ በእኛ ጉትጎታ ጥናት ተጀመረ። ሠራተኛው በየደረጃው የማታ ትምህርት እንዲከታተል ታስቦ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በባንኩ እርዳታ የማታ ትምህርት የሚያስተምሩ ምሁራን ተቀጠሩ። የባንክ ሠራተኞች ከጀመሩ በኋላ ከሌሎችም መንግሥታዊ ድርጅቶች ብዙ የማታ ተማሪዎች ተመዘገቡ። በባንክ ድጋፍ የተጀመረው ተቋም ነው ተስፋፍቶ የዩኒቨርስቲው ኤክስቴንሽን የደረጀው።

ሥራው እየተስፋፋ ቅርንጫፎቹ እየበረከቱ ሲሄዱ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ከንግድ ትምህርት ቤት ምሩቃን መቅጠር ጀመረ። የሰለጠነ የሰው ኃይል የእድገት መሠረት በመሆኑ የባንኩን የሰው

ኃይል ለማጠናከር ባንኩ የራሱን ማሰልጠኛ ተቋም ለማቋቋም ወስኖ በ1955 ዓ.ም. የለንደን የባንክ ባለሙያዎች ተቋም (THE LONDON INSTITUE OF BANKERS) ዋና ጸሐፊ የነበሩትን ሚስተር ሞሪስ ማግራ (MR. MAURICE MEGARAH) በመጋበዝ አስጠንቶ ለባንክ ድርጅቶች ተስማሚ የሆነ የባንክ ጥናት ተቋም (INSTITUTE OF BANKING STUDIES) ከፈተ። ይህ ነው ከዓመታት በኋላ አንድወጥ የሆነ የባንክና የመድህን ተቋም የሆነው።

የባንክ ስልጠና ተቋማት መኖር ብዙ ጠቀሜታ አለው። አንደኛው የሠራተኞቹን ምርታማነት ስለሚያጠናክር ወጪውን በመቀነስ ድርጅቱን ለውድድር ብቁ ያደርገዋል። ሁለተኛውና መሰረታዊ ሆኖ የሚታየኝ የነዚህ ዓይነት የስልጠና ጥረቶች ከፍላጎታችንና ከአቅማችን ጋር የተመጣጠነ የአሠራርና የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከል ከመሆኑ ሌላ የሀገራችንን እድገት ከማያዛልቅ የውጭ ጥገኝነት አላቆ አገር-በቀል በሆነና ዘላቂነት ሊኖረው በሚችል መሰረት ላይ ሊገነባ መቻሉ ነው።

በተጨማሪም ይኸ ስልጠና የሠራተኞቹን የሙያ ብቃት በማሳደጉ ባንኩ በየጊዜው ላስመዘገባቸው ከፍተኛ የሥራ ውጤቶች ዋናው ምክንያት ከመሆኑ ሌላ በአገሪቱ ያሉትን የገንዘብና የመድን ድርጅቶች የሰው ኃይል እጥረት ለመሸፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉ እሙን ነው። የዘወትር አሠራር የረቀቀ በመሆኑ በዚህ ዓይነት በየዘርፉ የሚሰጥ የማሰልጠኛ ተቋም በእኛ ጊዜ እንደጠቀመው አሁንም በጣም አስፈላጊ ይመስለኛል።

በዚህ ዓይነት ስልጠና የባንክ ሙያውን ብቻ ሳይሆን ከሙያው ጋር አብረው መሄድ ያለባቸው ቁም ነገሮች ማለት ትዕግስት ሰፊ የሆነ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ ለበጎ ምግባር መጨነቅን፣ ትክክለኛ የሆነ የባንክ ደምበኛና ሠራተኛ አያያዝን ማሰብና ማዳመጥ ነበር። ከአገር ውስጥ ስልጠናው በተጨማሪ ብቁ የሆኑት ሥራ አስኪያጆችና የአመራር ኃላፊዎች እየተመረጡ አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ኢጣሊያና እንግሊዝ አገር በሚገኙት ታላላቅ ባንኮች ከእኩያቸው ጋር እየሠሩ እንዲለማመዱ ይላኩ ነበር። ከሥራው ልምምድ በላይ ከመሰል

አገሮች ከሚመጡ የባንክ ዋና ሥራ አስኪያጆች የብድር መምሪያ ኃላፊዎች በሚሰጡ ሴሚናሮች ይሳተፉ ነበር። በዚህ ዓይነት እውቀታቸውን ማዳበር ከመሰል ባለሙያዎች ጋር ለማወዳደር ዕድል ነበራቸው።

ይህ ሁሉ የነበረውን የሥልጠና ዘዴ የምዘረዝረው በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በጣም አስፈላጊ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡ የባንክ አሰራር በፈጣን እርምጃ እየተለወጠ የሚሄድ በመሆኑ ዘመናዊው የአሰራር፣ የአስተዳደር፣ የአመራር ዘዴዎች በመቅሰም ስልቱ ሠራተኛውን ተዋህዶት የሙያ ብቃትና ቀልጣፋነት እንዲኖረው እጅግ በጣም አስፈላጊ ይመስለኛል።

## 4.2 የንግድ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት ሕንፃ ምረቃ

የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ሕንፃ እ.ኤ.አ. ኅዳር 16፤1915 ዓ.ም. በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተመርቆ ሲከፈት ከባንኩ ጋር ግንኙነት ላላቸው ሁሉ ታሪካዊ ግርማ የተሞላበት አስደሳች ጊዜ ነበር። በዚሁም የምረቃ ሥነ ሥርዓት ከብዙ የውጭ አገር የመጡ የባንክ ባልደረቦች ተገኝተውበት ነበር።

በተጨማሪ ከ1944 እስከ 1949 የቀድሞው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ገዥ የነበሩት ሚስተር ጆርጅ ኤ. ብላወርሰን፤ እንዲሁም በዚያን ጊዜ የኒው ዮርክ ፌደራል ሪዘርቭ ባንክ ምክትል ፕሬዚደንት የሆኑት ከ1953 እስከ 1957 የቀደመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ገዥ የነበሩት ሚስተር ዋልተር ኤች ሮዜል፤ እና በአርጀንቲና የፈርስት ናሺናል ሲቲ ባንክ ኦፍ ኒው ዮርክ ምክትል ፕሬዚደንት የነበሩትን ከ1945 እስከ 1949 የቀድሞው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ሚስተር ቪ. ኦፕሮልን የንግድ ባንኩ የክብር እንግዳ በማድረግ በሥነ በዓሉ ላይ በመገኘታቸው የሁሉም ደስታ የተለየ ነበር።

የንግድ ባንክ እያደገ የሚሄድ ለመሆኑ በሚገባ የሚያመለክተው ኅብኞችን የሚያስደስትና ከተለመደው ውጭ በሆነ አኳኋን የተቀየሰው

*የባንኩ ክብ ሕንፃ ከብዙዎች አድናቆት አትርፏል፤ በጎ ምኞትም አግኝቷል።*

*በዚህ የባንክ ምረቃ በዓል ላይ ከታደሉት የመታሰቢያ ስጦታዎች በተለይ የተቀረጹት የብርና የመዳብ መታሰቢያ ሜዳዮች፤ እንዲሁም በዚህ ዕለት የወጡት የማስታወሻ የፖስታ ቴምብሮች ዓይነተኛ ውብ በመሆናቸው እጅግ በላቀ አኳኋን ደስ ብሎት ያልተቀበለ ሰው አልነበረም።*

## 4.3 የ25ተኛው እና የ30ኛው ዓመት ክብረ በዓል

*የንግድ ባንክ እ.ኤ.አ. በኅዳር ወር በ1968 "የብር ኢዩቤልዩ" በድምቀት አክብሯል። ቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ይባል የነበረውና አሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሆነው የተቋቋመበትን ሃያ አምስተኛ ዓመት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት ተከብሮ ዋለ። ባንኩ በዘመናዊ ዕቅድ በተሠራው ሕንጻውና ቅርንጫፎቹ የጊዜውን ሁኔታ በመከተል ለደንበኞቹ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያደርገውን ጥረት ንጉሠ ነገሥቱ እየዞሩ በመጎብኘት በጣም ተደስተው ነበር።*

*የቀደመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የአሁኑ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁለቱም በኢትዮጵያ ውስጥ የአገሪቱ ኤኮኖሚ እንዲዳብርና በተለይም የንግድ፣ የእርሻና የኢንዱስትሪ ሥራ ይበልጥ እንዲስፋፉ ባለፈው 25 አመታት ውስጥ እርዳታ አድርገዋል። ይሁን እንጂ የባንኩን አገልግሎት ለአብዛኛው ሕዝብ ለማዳረስ ብዙ እንደሚቀር እሙን ነው።*

*ባንኩ ያስገኘውን ፍሬ በመመልከት ለባንኩ እድገት የደከሙትን የቀድሞዎቹን ሹማምንትና የባንኩ ወዳጆች ሁሉ አስታውሰው አመስግነዋቸዋል። በተለይም ከንግድ ባንኩ ጋር ተባባሪ በመሆን የረዱትን በልዩ ልዩ አገሮችም የሚገኙትን ወዳጅ ባንኮች ምስጋና ቀርቦላቸው ነበር።*

አጥብቄ የማስታውሰው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተለየ ድምቀት በ1973 ዓመተ ምህረት ያከበረውን የ30ኛውን ዓመት ክብረ በዓል ነው። አጋጣሚ ሆኖ እ.ኤ.አ. በ1973 ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) እና የዓለም ባንክ (WORLD BANK) ዓመታዊው ስብሰባ አፍሪካ ውስጥ ናይሮቢ ከተማ የተደረገበትን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የበዓሉን ቀን አሸጋሽገን እንዲገጥም አደረግንና ከታወቁ ባንኮች በመጻጻፍ ወደ አንድ መቶ የሚሆኑ ከባንካችን ጋር ቅርብ ግንኙነት የነበራቸውን የባንክ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከናይሮቢ የመልስ ጉዟቸውን በአዲስ አበባ በኩል እንዲያደርጉ አግባብተን ለባንካችን በዓል ጋበዝናቸው።

በዚህ አጋጣሚ ነው የአውሮፓና የአሜሪካ ታላላቅ ባንክ ፕሬዚደንቶች አገራችንንና ባንካችንን በመጎብኘት የንግድ ባንክን በዓለም መድረክ ታዋቂ ድርጅት ሆኖ እንዲታወቅ ያደረጉት። እንግዶቹ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ አውሮፕላን ተከራይተን በተቀነባበረ ፕሮግራም ባህርዳርን፣ ጎንደርን ላሊበላንና ሐረርን አስጎበኘናቸው። በሄዱበት ሁሉ የባንኩን ኃላፊዎች ቀልጣፋነት የገጠር ቅርንጫፎቹን ዘመናዊነት በማየት አደነቁ። ባንኩም ይበልጥ ታዋቂና ዝነኛ መሆን ቻለ።

ጎብኝዎቻችን በተለይ ደግሞ የተገረሙት የባንኩ አስተዳደር ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ነበር። በዚያን ጊዜ አፍሪካ ውስጥ የነበሩት ባንኮች አብዛኞቹ የሚመሩት በውጭ አገር ዜጎች ስለነበሩ ነው። በተጨማሪ የንግድ ባንክ ጎብኝዎችን እጅግ ያስደሰታቸው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ እንግዶቹን ቤተ መንግሥት ተቀብለው ብዙዎቹን በማነጋገር የተለየ የሻምፓኝ ግብዣ ስላደረጉላቸው ነበር።

## 4.4 የቅርንጫፎች መስፋፋት

በ1960ዎቹ ዓመታት ነው የባንኩ ቅርንጫፎች መከፈት በጣም የተፋጠነው። በየከተማው አዳዲስ የባንክ ቅርንጫች መከፈት በአገር ውስጥ ንግድ እንዲሰራጭ ረድቷል። ከሌሎች የግል መሰል

ድርጅቶች ጋር እኩል በመወዳደር ሥራውን እያሰራጨ ሕዝብን በመርዳት ሀገሪቱ ለምታደርገው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ጠቃሚ አገልግሎት አበርክቷል። ለህዝብ አገልግሎት መስጠቱ ጠቃሚ ቢሆንም ገንዘብ ጥቅም በሚያስገኝ ሥራ ላይ ውሎ ትርፍ እንዲያስገኝለት መጣሩም ተግባሩ ነው። ይህ ዓላማ ለመንግሥት ተጨማሪ ገቢ ከማስገኘቱም ሌላ የድርጅቱን የሥራ ክንውን የቀለጠፈና የተሟላ ያደርገዋል።

የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች አውታር ከጊዜ ወደ ጊዜ በማስፋፋት የንግድ ባንክ የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎትና የንግድ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በአገሪቱ ውስጥ እንዲሰራጭ በማድረግ ረድቷል። ይህ አይነቱም የሥራ አገልግሎት ለልማት መሠረታዊ ዓላማ የሆነውን የእርሻ፣ የንግድና የመገበያያ አቋም በበለጠ ሊያሻሽለውና ሊለውጠው ችሏል።

አዳዲስ ቅርንጫፎች የሚከፈቱት አማካይ ስፍራዎች በማጥናት ነው። በጥናቱም የሚካተተው የንግድ እንቅስቃሴ የኢንዱስትሪ እድግትና የሕዝብ ብዛት ነበር። የባንክ ቅርንጫፎች የሚከፈቱት ይህን አሟልተው በሚገኙ አማካይ ስፍራዎች ነበር። በዚህ በተፋጠነ እርምጃ ቅርንጫፎቹን አከታትሎ በመክፈት በ1961 ዓመተ ምህረት ገደማ የባንኩ የቅርንጫፎች ቁጥር 65 ደርሶ ነበር። ምንም እንኳ የቅርንጫፍ አውታር በመዘርጋት የሚወጣው የካፒታል ውጪ ገንዘብና የሠራተኞች ስልጠና ከባድ ሆኖ ቢገኝም ወደፊት ለባንኩ ተቀማጭ ሀብት መሆኑ አያጠራጥርም።

ቅርንጫፎች ለመክፈት የተደረገው እሽቅድምድም ህዝቡ ዘንድ የሚገኘውን ገንዘብ ለመሰብሰብ ብቻ ሳይሆን በቅርንጫፎቹ አማካይነት ገንዘብ ለሚሹ ተበዳሪዎች ብድር ለመስጠት ነበር። በየጠቅላይ ግዛቱ የራሳቸው ቤትና ቦታ ያላቸው ሰዎች አነስተኛ የንግድና የኢንዱስትሪ ሥራ ላይ ለተሰማሩት ሁሉ ገንዘብ በማበደር ጠቃሚ አገልግሎት አበርክቷል። ይህም እርምጃ ቀስ በቀስ በኢኮኖሚ አቋም ላይ ለውጥ ማስገኘቱ ግልጽ ነው።

ምንም እንኳ ባንኩ የነበረበት ውድድር ብርቱ ቢሆንም የባንኩ የክፍለ ሀገር መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ባበደሩትም ሆነ ሊሰበስቡ በቻሉት ገንዘብ ላይ እድገት ለማሳየት ችለዋል። ይኸም ሲወርድ ሲዋረድ አሁን ባለበት ደረጃ አድርሶታል። ስለዚህ ባንኩ አገሪቱ ውስጥ ራቅ ካሉ ቦታዎች ሁሉ ግንባር ቀደም ሆኖ ቅርንጫፎች መክፈቱን ለዓመታት አላቋረጠም።

በአገር ውስጥ የተቋቋሙት የባንክ ቅርንጫፎች ሲበረክቱ ለአስተዳደርና ለሥራ ቅልጥፍና በሚያመችና ለመገናኛ በሚቀል አኳኋን ቅርንጫፎቹን በክፍለ አገር ደረጃ አዋቀርን። ቀድሞ የነበሩትንና አዲስ የሚቋቋሙትን የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ደረጃ በደረጃ በማሰባሰብ ለመምራት በሚያስችል አማካይ (REGIONAL AREA) አስተዳደር ተደረገ። ይህ ድልደላ ለቁጥጥር የሚያስችል ሆኖ ለዘለቄታው እድገት መልካም መሰረት ሆነ።

ንጉሠ ነገሥቱ የባንኩን መስፋፋት ይደግፉ ነበር። ክፍለ አገር ሲጎበኙ አዲስ የተቋቋመውን የባንኩን ቅርንጫፍ መመረቅ ደስ ይላቸው ነበር። አንዱን ቅርንጫፍ ሲመርቁ በጊዜው ካደረጉት ንግግር እጠቅሳለሁ።

"ኢትዮጵያ የባንክ አዋጅን ካወጅን ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ በባንክ አሠራር ብዙ መሻሻል ተደርጓል። ባንኩ ከተቋቋመ ጀምሮ ባከናወነው ሥራ ስሙን በመልካም እያስጠራ ለመራመድ ችሏል። ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ የባንክ ድርጅት ኢትዮጵያ የምታደርገውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሁሉ በማበረታታት መልካም ስምና ዝና ማትረፉ ግልጥ ነው። ለወደፊትም የመሻሻል እርምጃ በዚህ አኳኋን እንደሚቀጥል ተስፋን እናደርጋለን።"

## 5. የንግድ ባንክ ጥገኛ ድርጅቶች

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባንድ በኩል ተወዳዳሪዎቹን ለመቋቋም በሌላ በኩል ደግሞ ኤኮኖሚው የሚያስፈልገውን እርዳታ ሁሉ ለማድረግ የጀርመኖች ባንኮችን ሞዴል በመከተል ሁሉንም ዓይነት የባንክ አገልግሎት የመስጠት ዝንባሌ እየተከተለ ነበር። ይህንንም

የምናደርገው በቀጥታ ወይም በጥገኛ ድርጅት ሲያስፈልግም በዘርፍ ኩባንያዎች አማካይነት ነበር። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አብዛኛውን አክሲዮን በመያዝ ያቋቋማቸው ጥገኛ ኩባንያዎች የሚከተሉት ነበሩ፡-

## 5.1 የኢትዮጵያ ንብረት ማልሚያ ኩባንያ አክሲዮን ማኅበር

የኢትዮጵያ ንብረት ማልሚያ ማኅበር የንግድ ባንክ ጥገኛ ኩባንያ ሆኖ የተቋቋመው እ.ኤ.አ. በሐምሌ ወር 1967 ዓመት ነው። እንደተቋቋመ የተረከበው የቀድሞ መንግሥት ባንክ በቁጠባና ብድር ክፍል ለቤት ማሠሪያ የሰጠው ሞርትጌጅ ብድርና በልዩ ልዩ ዓይነት ሥራ በሰው ዋስትና የተሰጠ ብድር ነበር።

የቤትና የሕንፃ ሥራ እየጨመረ የሚሄድ እንቅስቃሴ ነው። ችግሩን ለመቋቋም የንብረት ማልሚያን ኩባንያ የሚሰጠውን ብድር ማጠናከር ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ሊሆን የሚችለው የኩባንያው የገንዘብ አቋም ሲደረጅና ሲጠናከር፣ የሕዝቡ የቁጠባ ልምድ ሲደረጅ ነው።

ጥገኛ ኩባንያው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ንብረት በመሆኑ ድርጅቱ ራሱን ችሎ እንዲተዳደር ለማድረግ በተቻለ መጠን ይጥር ነበር። ይህንንም ዓላማ በመከተል ከአንድ ዝነኛ ከሆነ የኢጣሊያን ቁጠባ ድርጅት ጋር ልዩ ስምምነት ተደርጎ ነበር። በስምምነቱም መሠረት ይህ የውጭ አገር ድርጅት የንብረት ማልሚያ ኩባንያው በሚያደርገው ሰፊ የሥራ ፕሮግራም ተካፋይ እንዲሆን ሲደረግ ኪባንያውም ስሙን በመለወጥ "የቁጠባና የንብረት ማልሚያ ድርጅት" ተብሎ እንዲጠራ ተወስኖ ሥራ ላይ ዋለ። በዚህ ርዳታ መሠረት በሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት ድርጅቱ መልካም እድገት አስመዘገበ።

የኢትዮጵያ የቁጠባና የንብረት ማልሚያ ኮርፖሬሽን የብድር ሥራው ሲጠናከርና ራሱን ችሎ መስፋፋት ሲጀምር የራሱን ሕንፃ ሠንጋ ተራ ሰፈር አውራ ጎዳና ባለሥልጣን ሕንፃ አሠርቶ ሲጠናቀቅ ሚላን የሚገኘው ታላቅ የኢጣሊያን የቁጠባ ባንክ (CASSA DI RISPARMIO DELLE PROVINCE LOMBARDE) ሕንፃን ለማጌጥ

የሚረዳ የቢሮ ዕቃና መሳሪያ በእርዳታ መልክ አቀረበ። አዲሱ ሕንፃ ተመርቆ የተከፈተው በ1964 ዓ.ም. የላይቤሪያው ፕሬዚደንት ክብሩ ዶክተር ቶልበርት ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሁለቱ በተገኙበት ደማቅ ክብረ በዓል ላይ ነበር።

## 5.2 የንግድ ተጠሪ ማህበር

ባንኩ አንድ "ኮመርሻል ኖሚኒስ" (ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር) በሚል ስም ድርጅት አቋቁሟል። ድርጅቱ በአገሪቱ ሕግ መሠረት የግል ሰዎች ወይንም የኩባንያዎች ወኪል ወይም ተጠሪ በመሆን አክሲዮን፣ በአንድ ወይም በሌላ መልክ የሚቀርቡትን የገንዘብ ግዴታዎች በመቀበል፣ በመያዝ፣ በማስተዳደርና በመሸጥ ደንበኞቹን እንዲያገለግል ነው። ከዚህም በላይ በአደራ የተሰጡትን ንብረቶችና የሙት ሀብቶች በሚቹ ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት በማስተዳደርና በማከፋፈል የአደራ ጠባቂነትን የኑዛዜ አስፈጻሚነትን ወይም የንብረት አስተዳዳሪነትን ሥራ ሁሉ ተቀብሎ ደንበኞቹን ያገለግላል።

ንብረት በአደራ የማስተዳደር ክፍል ለማኅበራዊ ኑሮአችን ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ በመሆኑ ሕዝቡ ጥቅሙን እያወቀ ሲሄድ አገልግሎቱ ይስፋፋል ብሎ በመገመት ነበር ተጠሪው ድርጅት የተቋቋመው። በጥናታችን መሠረት የሞቱ ሰዎችን ንብረት ማሰባሰብ ሂሳብን ማዘጋጀት ባንኩ የሚሰጠው አገልግሎት የማያቋርጥ በመሆኑ ጠቃሚነቱ የታወቀ ነው። ነገር ግን የ1966 አብዮት በግል ንብረት አያያዝ ከፍተኛ ለውጥ ስላመጣ የድርጅቱ ሥራ ውስን ሆኖ ቀረ፡፤

## 5.3 የባሕርና የትራንዚት አገልግሎት (አ.ማ.)

የባሕርና የትራንዚት አገልግሎት (አክሲዮን ማህበር) የባንኩ ጥገኛ ድርጅት ሆኖ የተቋቋመው እ.ኤ.አ. በ1968 ዓመት ላይ ነበር። ሥራው ከኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የተወረሰ ነው። የማኅበሩ ካፒታል 500,000 ብር ሆኖ የንግድ ባንክና የንብረት ማልሚያ ድርጅት አንድነት የማኅበሩን ካፒታል 80% ድርሻ ይዘው የቀረውን ድርሻ ደግሞ የፈረንሳይና የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩባንያ ነበር።

ይህ ኩባንያ ቀድሞ በጂቡቲ በአዲስ አበባና በአሰብ በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ በኋላም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይካሄድ የነበረውን የትራንዚት የዕቃ መላክና የመጋዘን ሥራ (BONDED WAREHOUSE) ተረክቦ ያከናውን ነበር። ኩባንያው የተመሰረተው ወደፊት ሥራው እየተስፋፋ ሲሄድ ለንግድ ባንክ ደንበኞችና ለሌሎችም በሸቀጥ አስመጪና ላኪነት ሥራ ለተሰማሩት ሁሉ ጠቃሚ አገልግሎት ከመስጠቱ ሌላ በጅቡቲ በአሰብና በምፅዋ ወደቦች ለሚጠቀመው ሁሉ በጣም ጠቃሚ አገልግሎት ይሆናል ተብሎ ተገምቶ ነበር። ከአብዮቱ በኋላ እቅዱ ተለወጠ። በደርግ አገዛዝ ዘመን ማኅበሩ ከሌሎች ከተወረሱ የትራንዚት ድርጅቶች ጋር ተዋህዶ አንድ ብቸኛ የመንግሥት የባሕር አገልግሎትና የትራንዚት ድርጅት ሆኖ ሥራውን ቀጠለ።

## 6. የነበረው የኢኮኖሚና የንግድ ሁኔታ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ያደረገውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለመገመት በጊዜው የነበረውን የእድገት ደረጃ ማስታወስ ይረዳል።

በእኛ ዘመን አገሪቱ ስትከተል በአመዛኙ የነፃ ገበያ ሥርዓትን ሆኖ ዘላቂ ጥቅሟን የሚንከባከብና በተወጠነለት የእድገት አላማ የምትመራ ሥርዓት ነበራት። አገሪቷ የነበራትን አነስተኛ ወረት ከውጭ ከሚገኝ እርዳታና ብድር ጋር ተቀናጅቶ ከፍተኛ እድገት ሊያመጡ በሚችሉ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያውል በየአምስት ዓመት የሚዘጋጅ የልማት ፕላን ነበራት። በ1950ዎቹ መካከል ዓመታት የተጀመረው ይህ የአምስት ዓመት የፕላን ምዕራፎች በዘመኑ የማይናቁ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥና እድገት አሳይቷል። በተለይም በሁለተኛውና በሦስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ዘመናት አገሪቷን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለመሸጋገር ይረዳል ተብለው የተቋቋሙ ፋብሪካዎች እያደጉና እየጎለበቱ ሲሄዱ ነው የጥቅም ልዩነት እየጎላ የመጣው። በመንግሥት አካላትና በንግዱ ኅብረተሰብ መሐከል ከፍተኛ የመተጋገዝና የመረዳዳት መንፈስና ፍላጎት ነበር። ይህ ትብብር ነበር የማይናቅ እድገት ያመጣው።፡

በንጉሡ ዘመን የነበረው የኢኮኖሚ ይዞታ "የጠራ ውድድር" ባይሆንም የግል ንብረትና ይዞታ የሰፈነበት ወቅት ነበር። በሚሰጠው የአጭርና የረጅም ጊዜ ብድር የንግድ ባንክ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። አገር ውስጥ ከነበሩት ዋና ዋና ኢንዱስትሪዎች የንግድ ድርጅቶች አብዛኞቹ የቅርብ ግንኙነት ነበራቸው። ለሥራ ማስኬጃ፣ ለዕቃ ማከማቻና ለውጭ ንግድ በተንቀሳቃሽ ሂሳብ (ኦቨርድራፍት) በቋሚ ብድር ከንግድ ባንክ የማይፈልግ አልነበረም። እርግጥ ነው በጊዜው የነበሩት ባለሀብቶች አብዛኞቹ የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። ባንኩ ብድር ሲሰጥ የሚያመዛዝነው የዋስትናውንና የሥራ ብቃቱን ነበር።

በአሁኑ ጊዜ የብድሩን አሃዝ ማንሳቱ አይጠቅምም፤ የኢንዱስትሪዎቹን ስምና ተግባር እጠቅሳለሁ፡- የዳርማርና የአስኮ ኩባንያ፣ የቆዳ ማልፊያና የጫማ ፋብሪካዎች፤ የድሬዳዋ፣ የባሕር ዳር፣ የዲያባኮ፣ የላዛሪዲስ፣ የባርቶሎ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች፤ የኮካ ኮላ፣ የማባ ጠጅ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስና የሜታ አቦ የቢራ ፋብሪካዎች ሁሉ የባንኩን ድጋፍ ይፈልጉ ነበር። በንግዱም በኩል የባንኩ ድጋፍ ወሳኝ ነበር። ከታላላቅ አስመጪ ኩባንያዎች ቤላ ኩባንያ፣ ሚቸልኮት፣ ፖል ሪየስ እና ሰፈሪያን ኩባንያ። ከቡና ላኪዎች ከድር ኤባ፣ ኮታሪ፣ ተድላ ደስታ፣ ኪዳኔ በየነ ከማስታውሳቸው ጥቂቶቹ ናቸው።

የንግድ ባንክ ለሕዝብ ከሚያቀርበው የባንክ አገልግሎት ሌላ ከብሔራዊ ባንክ ጋር በመተባበር የሀገር ውስጥ መጠነኛ የአክሲዮን ገበያ አቋቁሞ ነበር። ይህን የአገር ውስጥ የአክሲዮን ገበያ ለማስፋፋት ብዙ እቅድ ነበረው። ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ገንዘባቸውን ጥቅም በሚያስገኝ ሥራ ላይ እንዲያውሉ ባንኩ ያበረታታ ነበር። ገንዘብ ያላቸው ሰዎች የአክሲዮንን ጥቅም ተረድተው ገንዘባቸውን በዚህ ተግባር ላይ ካላዋሉ ደንበኛ የካፒታል ገበያ ሊያስፋፉ አይችሉም። በዚህ ዓይነት ጥቂት መሻሻል ቢታይም ገንዘቡን አክሲዮን ግዢ ላይ ለማዋል የሚፈልገው ሕዝብ ብዙ ምርጫ እንዲኖረው ለማድረግ በገበያው ላይ የሚሸጡትንና የሚገዙትን አክሲዮኖች ማብዛት ያስፈልጋል።

ቀደም ብዬ እንደገለጽሁት በዚያን ዘመንና በተለይም ከ1955 እስከ 1965 ዓ.ም. ድረስ በነበሩት አስር ዓመታት ከፍተኛ የልማት ተግባራት ተካሂደዋል። በእነዚህ ዓመታት የተሠሩትን ሥራዎች ሳስታውስ ሁለት ቁም ነገሮች ውል ይሉብኛል። አንደኛው በመንግስትና በንግዱ ኅብረተሰብ መካከል የአላማ አንድነት መኖር ከታመነበት የእነዚህ ሁለት አካላት ይህን በመሰለ የትብብርና የአላማ አንድነት ከተሠራ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአገሪትዋ ከፍተኛ ለውጥ ልታስመዘግብ ትችላለች። ሁለተኛው በዚያን ጊዜ የነበረው የልማት ጥረት ቢቀጥል ኖሮ እያልኩ አንዳንዴ የሚመጣብኝ ቁጭት ነው።

አንዳንዴ ወዳለፈው ዘመን መለስ ብዬ ስመለከት በእኛ የሥራ ዘመን የጎደለው ቆራጥነት ይመስለኛል። በነበረን ሰፊ የአስተዳደር ስልጣን በድፍረት ብዙ ሊሠራ ይችል ነበር። ሲያስፈልግም አስረድተን፣ ጠቀሜታውን አሳውቀን ሽንጣችንን ገትረን ብንከራከር ኖሮ የተሻለ ለውጥ አምጥተን የተሻለ አገር ለተተኪው ትውልድ እናስረክብ ነበር።

የአገሮች የኢኮኖሚ ዳርና ድንበር ለማፍረስ ዓለምን አንድ ወጥ ለማድረግ የሚደረገው እንቅስቃሴ በእጅጉ እየተፋፋመ ነው። ስለዚህ የዛሬው የምርት ዓለም እኛ ከነበርንበት በጣም ተለውጧል። እኛ ስንመካባቸው የነበሩት አስተማማኝና ፈጣን የግንኙነት መስመሮች ኋላ ቀር ሆነዋል። ዛሬ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ መረጃ የሚተላለፈው ከመቅፅበት ሆኗል። ገኸርና ሻጭ፣ ባንክና ደንበኛ ለመገናኘት በደላላና ባገናኝ መማሰኑ ቀርቶ ኢንተርኔትን ወደ ማገላበጥ ተለውጧል።

በአሁኑና በእኛ ዘመን ያለው ትልቅ ልዩነት የገበያ ጉዳይ ነው። አገራችን የነበሩት ኢንዱስትሪዎችና በኋላም በግብርናው ዘርፍ የነበረው ችግር የምርት ሳይሆን የገበያ እንደነበር የታወቀ ነው። ገበያን ለማስፋፋት አገር ውስጥ ብዙ ጥረት ነበር።

## 7. መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሕዝባዊ አገልግሎት አላማው ንጉሣዊ ድጋፍ ነበረው። አፄ ኃይለ ሥላሴ ለባንኩ ልዩ አስተያየት

ነበራቸው። የባንኩን ቅርንጫፍ በመረቁ ቁጥር በሚያደርጉት የምረቃ ንግግር ላይ በባንኩና በሕዝቡ መሐከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ሲናገሩ "የሕዝብ በጎ ፈቃድና መተማመን በየዕለቱ መረጋገጥ አለበት" ይሉ ነበር። በተለይ በ1960 ዓ.ም. የአዲስ ከተማውን ዋና ቅርንጫፍ ሲመርቁ እንዲህ ብለው ነበር፦ "በኢትዮጵያ የባንክ አዋጅ ከአወጅን ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ በባንክ አሠራር ብዙ መሻሻል ተደርጓል። ባንኩ ከተቋቋመ ጀምሮ ባከናወነው ሥራ ስሙን በመልካም እያስጠራ ለመራመድ ችሏል። ከዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ ባንክ ድርጅት ኢትዮጵያ የምታደርገውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሁሉ በማበርታት መልካም ስምና ዝና ማትረፉ ግልጥ ነው። ለወደፊትም የመሻሻል እርምጃ በዚህ አኳኋን እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን።"

መቼም በዚህ ዓለም ሁሉ ነገር ሰው እንዳሰበው አይሆንምና በ1966 ዓ.ም. ያልታሰበ ለውጥ መጣ። ድንገት አብዮት ፈነዳ፤ የነበረው ንጉሣዊ ሥርዓት ፈረሰ። መሬት የመንግሥት ሆነ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ተወረሰ። የግል ባንኮችና የመድን ድርጅቶች ተወርሰው በብሔራዊ ባንክ ስር ተሰባሰቡ። የንግድ ድርጅቶችና የግል ፋብሪካዎች ሁሉ ወደ መንግሥት ይዞታ ተዛወሩ። በወደቀው ሥርዓት ስር በአመራር ላይ የነበረውን ኅብረተሰብ ከፊሉ ተገደለ፣ ገሚሱ ታሰረ፣ ሌላው ከሥራ ተባረረ፣ ሌላው ደግሞ ተሰደደ። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ከዚህ ለውጥ ትርምስ አላመለጠም።

በደርግ ዘመን ማዕከላዊ የኢኮኖሚ አሠራር የተንሰራፋበት ጊዜ ስለነበረ ባንኮቹን ሥራ በሚያጨነግፍ በሞኖፖል አስሮ በመያዝ ቁጥጥሩ ተጠቃሎ ለብሔራዊ ባንክ ተሰጠ። በደርግ አገዛዝ ዘመን ድርጅቶች በነፃ እንዳይንቀሳቀሱ በጠበቀ ቁጥጥር ተያዙ ቅርንጫፎች የሚንቋቋሙበት የገበያ ጥናት መሆኑ ቀርቶ በባለሥልጣናት ፍላጎትና ትእዛዝ እየተደላደለ ነበር። የብድር ፖሊሲው የሚመራው የነበረውን ሶሻሊስታዊ ሥርዓትን ለማጠናከር ነበር። በዚህ ከባድ ተጽዕኖ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ፈራርሶ ከፍተኛ ውድቀት ደረሰበት።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2003 ዓመት የ60ኛ ዓመቱን ክብረ በዓል ሲያከብር በጊዜው የነበሩት የባንኩ ፕሬዚደንት አቶ ገዛኸኝ ይልማ፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ አመሰራረት አንስቶ ባንኩ የገጠመውን የእድገት ውጣ ውረድ አውስተው ያለፉትን የባንኩን ባለሙያዎች አስታውሰው በሚቀጥሉት ቃላት አሞግሰዋቸዋል፡- "ታሪክ ከማይረሳቸው ከእነዚህ ቀደምት የባንክ ባለሙያዎች መስዋዕትነትን፣ የዓላማ ጽንዓትን፣ ለአገር አሳቢነትን፣ ተቆርቋሪነትን፣ ታማኝነትን እኛ በአዲሱ ዘመን የምንገኝ ዜጎች ልንማር ይገባናል" ብለው ደምድመዋል።

እኔም ንግግሬን በሚከተለው ሃሳብ እደመድማለሁ። የዛሬ ስምንት ዓመት በ1991 ዓ.ም. ለአቢሲኒያ ባንክ ምረቃ ታጋብዤ በመጣሁበት ጊዜ በጦቢያ መጽሔት ተጠይቄ ቃለ ምልልስ ተለዋውጠን ነበር። መደምደሚያው ላይ ላገሬ ያለኝን ራዕይና ምኞት ተጠይቄ የሰጠሁትን መልስ አዘጋጆቹ አጠቃልለው እንዲህ ብለው መዝግበውት ነበር፡- "እኔ ለኢትዮጵያ የምመኘው ከጦርነት ውጥረትና ከሚያስከትለው ጥፋት አምልጠን በመልማት ላይ እንዳሉት ሌሎች አገሮች ወደ ልማቱና ማህበራዊ እድገት እንድትደርስ ነው። ለዚህ ደግሞ ራዕይ ያለው አመራር፣ ተግባብቶ የሚኖር ህዝብ፣ በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ የሚኮራና አገሩን የሚያስከብር ዜጋ መኖር ወሳኝ ነው።" ብዬ ነበር። አሁንም ምኞቴና ፀሎቴ ይኸው ነው።

# FSS Publications List

**[currently available in stock]**

## FSS Periodical

- *Medrek, now renamed FSS BULLETIN* (Quarterly since 1998. English and Amharic)

- *Africa Review of Books* (Managed by FSS for CODESRIA)
    - Vol. 1, No. 1 (October 2004)
    - Vol. 1, No. 2 (September 2005)
    - Vol. 2, No. 1 (March 2006)
    - Vol. 2, No. 2 (September 2006)
    - Vol. 3, No. 1 (March 2007)

| FSS Discussion Papers | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 8 | *Livelihood Insecurity Among Urban Households in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato and Aklilu Kidanu. 2002 | 20.00 |
| No. 9 | *Rural Poverty in Ethiopia: Household Case Studies from North Shewa.* Yared Amare. 2002 | 20.00 |
| No.10 | *Rural Lands and Evolving Tenure Arrangements in Ethiopia: Issues, Evidences and Policies.* Tesfaye Teklu. 2003 | 20.00 |
| No.11 | *Resettlement in Ethiopia: The Tragedy of Population Relocation in the 1980s.* Dessalegn Rahmato. 2003 | 20.00 |
| No.12 | *Searching for Tenure Security? The Land System and New Policy Initiatives in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato. 2004 | 20.00 |
| No.13 | *A Comparative Study of Forest Management in Eza District, Gurage Zone, Southern Ethiopia.* Tenkir Bonger. 2005 | 20.00 |

| FSS Monograph Series | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 2 | *Poverty And The Social Context of Sex Work In Addis Ababa: An Anthropological Perspective.* Bethlehem Tekola. 2006 | 40.00 |
| No. 3 | *Democratic Assistance to Post-Conflict Ethiopia: Impact and Limitations.* Dessalegn Rahmato and Meheret Ayenew. 2004 | 25.00 |
| No. 4 | *Development Interventions in Wollaita, 1960s-2000s: A Critical Review. Dessalegn Rahmato. 2007* | 35.00 |
| Special No. 1 | *Lord, Zega and Peasant: A Study of Property and Agrarian Relations in Rural Eastern Gojjam.* Habtamu Mengistie. *2004* | 30.00 |

| Consultation Papers on Poverty | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 3 | *Civil Society Groups and Poverty Reduction.* Abonesh H. Mariam, Zena Berhanu, and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. 2001 | 5.00 |
| No. 4 | *Listening to the Poor.* Oral Presentation by Gizachew Haile, Senait Zenawi, Sisay Gessesse and Martha Tadesse (in Amharic). Edited by Meheret Ayenew. 2001 | 5.00 |

| Gender Policy Dialogue Series | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 1 | *Gender and Economic Policy*. Edited by Zenebework Tadesse. 2003 | 10.00 |
| No. 2 | *Gender and Poverty* (Amharic). Edited by Zenebework Tadesse. 2003 | 10.00 |
| No. 4 | *Gender Policy Dialogue in Oromiya Region.* Edited by Eshetu Bekele. 2003 | 10.00 |
| No. 6 | *Gender Policy Dialogue in Southern Region.* Edited by Eshetu Bekele. 2004 | 10.00 |

| Consultation Papers on Environment | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.1 | *Environment and Environmental Change in Ethiopia*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.2 | *Environment, Poverty and Gender*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.3 | *Environmental Conflict*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. July 2003 | 10.00 |
| No.4 | *Economic Development and Its Environmental Impact*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.5 | *Government and Environmental Policy*. Consultation Papers on Environment. 2004 | 10.00 |
| No.6 | *የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል (የሰሜን ሸዋ ገበሬዎች ተሞክሮ)* Consultation Papers on Environment. May 2004 | 10.00 |
| No.7 | *Environmental Challenges of Contemporary Ethiopia and the Indispensable Role of Indigenous Trees*. Legesse Negash. 2004 | 10.00 |

| FSS Studies on Poverty | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.1 | *Some Aspects of Poverty in Ethiopia: Three Selected Papers.* Dessalegn Rahmato, Meheret Ayenew and Aklilu Kidanu. Edited by Dessalegn Rahmato. 2003 | 10.00 |
| No.2 | *Faces of Poverty: Life in Gäta, Wälo.* Harald Aspen. 2003 | 15.00 |
| No.3 | *Destitution in Rural Ethiopia.* Yared Amare. 2003 | 10.00 |
| No.4 | *Environment, Poverty and Conflict*. Tesfaye Teklu and Tesfaye Tafesse. 2004 | 10.00 |
| No.5 | *Issues in Urban Poverty: Two Selected Papers*. Daniel Kassahun and Meron Assefa. July 2005 | 10.00 |

| ከድህነት ወደ ልማት:- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ<br>**From Poverty to Development: Intergenerational Transfer of Knowledge** | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| **ቁጥር 1** | ***ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (1966-1983)::* ሽመልስ አዱኛ፣ 1997 ዓ.ም.** | 10.00 |
| **ቁጥር 2** | ***የአባይና የተፋሰሶቹ ዓለም ዓቀፋዊ ችግር::* ዘውዴ ገ/ሥላሴ፣ 1997 ዓ.ም.** | 10.00 |
| No. 2 | *The Blue Nile and Its Basins: An Issue of International Concern*. [English Version]. Zewde G/Sellassie. 2006. | 10.00 |
| **ቁጥር 3** | ***ትምህርት፣ ባህልና ዕድገት: የትዝታ ጉዞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እስከ ዓለም አቀፍ የኤኮኖሚ ተቋማት (1948-1996)::* አስፋው ዳምጤ፣ 1998 ዓ.ም.** | 10.00 |
| **ቁጥር 4** | ***ጆርናሊዝምና እድገት በኢትዮጵያ፤ የግል ትዝታዎች ከ1952 ጀምሮ::* ነጋሽ ገ/ማርያም፣ 1998 ዓ.ም.** | 10.00 |
| No. 5 | *National Air Carriers as Catalysts for Devleopment: The Case of Ethiopian Airlines (ET)*. Semret Medhane, 2006. | 10.00 |
| 2ኛ ዙር ቁጥር 1 | *አንጋፋው የኢንቨስትመንትና የግሉ ክፍለ-ኤኮኖሚ ተዋናይ:: ተካ ኤገኖ፣ 1999 ዓ.ም.* | 10.00 |
| 2ኛ ዙር ቁጥር 2 | *በኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ሂደት፣ ነባራዊ ሁኔታና የወደፊቱ ስጋት:: ጠና አበረ፣ 1999 ዓ.ም.* | 10.00 |
| 3ኛ ዙር ቁጥር 3 | *የኢንዱስትሪና የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር እድገት:: ተፈራ ኃ/ሥላሴ 1999 ዓ.ም.* | 10.00 |

| **Book Series** | Price (Birr) |
|---|---|
| • *Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below*. Edited by Bahru Zewde and Siegried Pausewang. Nordic African Institute, Uppsala and the Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2006 | 80.00 |

| **Environmental Documentaries on CD and Video** | Price (Birr) |
|---|---|
| • **የከተማችን አንባቢ ከየት ወደየት?** (Amharic Video Film) | 50.00 |
| • **ውጥንቅጥነ ድህነትና የአንባቢያችን መጎሳቆል** (Amharic Video Film) | 50.00 |
| • "Witinkit": Poverty and Environmental Degradation (CD in Amharic with English Subtitles) | 100.00 |

| **Proceedings** | Price (Birr) |
|---|---|
| • *Decentralization in Ethiopia. Edited* by Taye Assefa & Tegegne Gebre-Egziabher . 2007 | 51.00 |

| **Research Report** | Price (Birr) |
|---|---|
| • *Rainwater Harvesting in Ethiopia: Capturing the Realities and Exploring Opportunities. Daniel Kassahun. 2007.* | 25.00 |

## የማኅበራዊ ጥናት መድረክ

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) አትራፊ ያልሆነ፣ ልማት-ነክ በሆኑ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጥናት የሚያካሂድ ነፃ ተቋም ነው። ማጥመ በሕዝባዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ነፃ የውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፤ የሕዝብን ግንዛቤ ለማዳበር ይንቀሳቀሳል። በፖሊሲ ክርክሮች ውስጥ ሰፋ ያለ የሕዝብ ተሳትፎን ማዳበር ለዲሞክራሲው ሂደት ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብሎ ማጥመ ያምናል። ግቦቹን ለማሳካትም ማጥመ ዐውደ-ጥናቶችን ያዘጋጃል፣ የምርምር ውጤቶቹንም በማሳተም ለፖሊሲ አመንጪዎችና ሌሎች የመንግሥት አካላት፣ ለሲቪል ማኅበራት፣ ለባለሙያዎች፣ ለግሉ ክፍለ-ኤኮኖሚ አባላትና ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ እንዲሁም ለለጋሽ ድርጅቶች ያሠራጫል።

